


በመጀመሪያ መልካም የገና በዓልና አዲስ ዓመት እንዲሆንልዎ እንመኛለን። 2010 እድራችን የተመሰረተበት ዓመት ነውና በተለየ ሁኔታ የምናስታውሰው ነው። የእድር ምስረታው፤ ግንባታውና የአባላት ምዝገባ ሂደት ሁሉ ከምንጠብቀው በላይ መሳካቱ ሁላችንንም አስደስቶናል። የኮምንቲአችን ማኅበረሰብም በተለይም የማኅበራችን፤ የቤተ-ክርስትያኖቻችንና የበርካታ ግለሰቦች ድጋፍና ትብብር ለስኬቱ ዓይነተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል። ለወደፊትም ይህ እንደሚቀጥል እናምናለን። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እድሩ ያደረገውን የመጀመሪያ ጠቅላላ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ያገኛሉ። ቃለ ጉባኤው ከምስረታው ጀምሮ ስብሰባ እስከተደረገበት ግዜ (Nov. 7, 2010) ድረስ ያለውን የስራና የፋይናንስ እንቅስቃሴ ይገልጻል። ከዚያ ወዲህ የተከናወኑትን ተግባራትና የፋይናንስ ሪፖርት ደግሞ ተጠናቆ በወቅቱ ይላካል። ይህ ጽሑፍ ሲዘጋጅ ያለን ተቀማጭ ገንዝብ ከውስጥ ሰፍሮ ያገኙታል። ክፍያን በተመለከተ ብዙ አባላት በባንክ እየተጠቀሙ ስለሆነ አሰራሩን ቀና አድርጎታል። ይህንን ያላደረጋችሁ እንድታደርጉ ይሁን። በተለይም በኢንተርኔት ባንኪንግ መክፈል አመቺ ነው። ከቤትዎ ሳይወጡ የባንክ ስልፍ ሳያሰለችዎት 24 ሰዓት መጠቀም ይችላሉ። ባንክዎን በማነጋገር በዚህ መንገድ ቢከፍሉ ይመረጣል። እንግዲህ እድሩን ተባብረን ስለሆነ መገንባት የምንችለው ሃሳብ ካልዎት በአድራሻችን ይላኩልን። ግልጽ በግልጽ ሃሳብን አንስቶ መነጋገር ቀናነት ነው። በስራ ላይ የሚታይ ግድፈት ካለ፤ ሊጣራ የሚያስፈልገው ጉዳይ ካለ፤ ምላሽ የሚሻ ነገር ካዩና/ወይም ከስሙ ወዘተ... ለሁሉም ማብራሪያ ይኖረዋልና ከእድሩ አስተዳደር ጽ/ቤት ማንኛውንም አባል አግኝተው ማነጋገር ይችላሉ። በድጋሚ መልካም ግዜ እየተመኘን ጽሑፉን እንዲያነቡ እንጋብዛለን።

የኢትዮጵያ መረዳጃ እድር በሲድኒ
**P.O.Box 279 Auburn NSW 1835**
**ethiopianidir@gmail.com**
**0434287709**

# የመጀመሪያው ጠቅላላ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ

ቀን፡ ኖቬምበር 7 እሑድ
ቦታ፡ ሊድከም አዳራሽ
ሰዓት፡ 3 Pm

## አጀንዳዎች

### 1) የመግቢያ ንግግር (አቶ እስማኤል ሱሊማን)

እድሩን በማሰባሰብና እስከአሁንም ስራውን የሚያኪያሂደው ኮሚቴ ም/ዳኛ አቶ እስማኤል ሱሊማን የመጣውን ሕዝብ አመስግነው ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር "የምንኖረው በሰው ሀገር ሲሆን አብዛኛው ሕብረተሰባችን ግን የዕለት ተዕለት ኑሮውን ለማቃናት ደፋ ቀና ከማለት አልፎ የመኖርን ያህል መሞትም እንዳለ የተገነዘበው አይመስልም" ብለዋል። በዚህ አይነት ሁኔታ መቀጠልም ማብቃት ያለበት ጉዳይ እንደሆነም አስገንዝበዋል። ስለሆነም ብቸኛው አማራጭ የተመሰረተውን እድር በመደጋገፍ ማራመድና ማሳደግ የሁላችንም የትውልድ ኃላፊነት ነው በማለት አሳስበዋል።

### 2) ስለ እድሩ አመሰራረት፣ የእድሩ ዓላማ፤ ስለመተዳደሪያ ደንቡና ስለተከናወኑ ተግባሮች አጠቃላይ ገለጻ (አቶ ሰሎሞን ከበደ)

በመጋቢት ወር 2010 ውስጥ ከተለያየ አካባቢ የተውጣጡ የስድኒ ነዋሪዎች ተገናንተው እድር ለመመስረት ሁኔታዎችን አመቻቹ። ቀዳሚ ተግባር አድርገው የተነሱት ዓላማውንና ሊሰጥ የሚገባውን አገልግሎት የሚዘረዝር መተዳደሪያ ደንብ ማርቀቅ ነበር። ዓላማዎቹን ፀሃፊው አቶ ስሎሞን ከበደ እንደሚከተለው ገልጸዋል፤

1. በአባል ላይ ሐዘን ሲደርስ የችግሩ ተካፋይ በመሆን መተጋገዝ። ይህም የተመደበውን የገንዘብ መጠን መሰጠት እና ከቀብር ስርዓቱ ጋር ተጓዳኝ የሆኑ ስራዎችን በመስራት አገልግሎት መስጠት።
2. አንድ አባል ወይም የቤተሰቡ አባል ቢታመም ቤተሰቡ በሚፈቅደው መንገድ በመጠያየቅ መተጋገዝ።
3. የተለያዩ ዝግጅቶችን በማድረግ አባላትና ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲቀራረቡና እንዲጠያየቁ አጋጣሚዎችን መፍጠር።

የሚሉት ሲሆኑ መርዶን በተመለከተ ግን እድሩ ምንም ዓይነት አገልግሎት እንደማይሰጥ ጠቁመዋል።
ከዚህም በመቀጠል ግዚያዊው የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እስከዛሬ ድረስ በየወቅቱ ያከናወናቸውን ዋናዋና ተግባሮች በዝርዝር አቅርበዋል። (መጨረሻ ገጾች ላይ ስፍሯል)። አባላት ከእድሩ የሚያገኙት ጠቀሜታ፣ የአባላት መብትና ግዴታ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የሰፈሩትን ዋና ዋና አንቀጾች አብራርተዋል።

### 3) ፋይናንስ ሪፖርትና ስለ ክፍያ አሰባሰብ ዜዴዎች (አቶ ለማ ብሩና አቶ ግርማ ፈይሳ)

የፋይናንስ ሪፖርትና የተዘረጋውን ግልጽ የአሰራር ዘዴ በተመለከተ ገንዘብ ያዥና የፋይናንስ ኃላፊዎቹ አቶ ለማ ብሩና አቶ ግርማ ፈይሳ በቅደም ተከተል ገለጻ አድርገዋል።የፋይናንስ ሪፖርቱ እንደሚከተለው ቀርቧል።

| | | |
|---|---|---|
| | | |
| **እስከ አክቶበር 31ቀን 2010 ድረስ ያለው የገቢና ወጪ ዝርዝር** | | |
| **ገቢ** | | **3083.05** |
| *ከአባላት የተገኘ ክፍያ* | | |
| | | |
| **ወጪ** | | |
| *የአዳራሽ ኪራይ* | *110.00* | |
| *የፖስታ ኪራይ* | *83.45* | |
| *የእድር ምዝገባ (ፌርትሬዲንግ)* | *154.00* | |
| *ለፖስታ እና ስታምፕ* | *40.60* | |
| *ባንክ ያስከፈለው* | *30.00* | |
| | | |
| የውጪ ድምር | | **418.05** |
| | | |
| አሁን በባንክ ያለው የተጣራ ተቀማጭ | | **2,665.00** |

**(አሁን ማለትም በዲሴምበር 23 በባንክ ያለን የተጣራ ተቀማጭ ገንዘብ $5795.00 ነው።)**

በመተዳደሪያ ደንቡ እንደሰፈረውም የፋይናንስ ሪፖርት ማለትም ወጪና ገቢ እንዲሁም በየወቅቱ ያለው የእድሩ ካፒታል በጥሬ ገንዘብና ንብረት ለአባላቱ ወደፊት የገለጻል። በእለቱ ከአባላትና አዲስ ከተመዘገቡት በእጅ ከ$750 ዶላር በላይ ሲሰበሰብ ሌሎችም በባንክ እንደሚያስገቡ ገልጸዋል።

4) ***ሥነ-ግጥም ;*** የዕለቱን ስብሰባ ምክንያት በማድረግ ወ/ሮ ውብዓለም ያሊ ሥነ-ግጥም አቅርበዋል።

**በእረፍት** ግዜ የመዝናኛ ምግብና መጠጥ (Refreshment) ቀርቧል።

5) **ምርጫ**

አሁን ያለው ኮሚቴ ግዚያዊ በመሆኑ ቋሚ ኮሚቴና የመካሪ ጉባኤ አባላት እንዲመረጡ የስብሰባው መሪ አቶ እስማኤል አጀንዳውን ከፍተዋል። አባላት ሃሳብ እየሰጡ ይህ ኮሚቴ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲያገለግልና የተጀመረው ስራ እንዲጠናቀቅ መቀጠል አለበት ብለዋል። በሌላ በኩልም የኮሚቴ አባላቱ ስብጥር ኅብረተሰቡን በሰፊው የሚወክሉ ሆኖ ስለሚታይ በዚሁ ይቀጥሉ የሚሉና ተመሳሳይ ድጋፎች ተሰንዝረዋል። ያሉት 8 የኮሚቴ አባላት እንዳሉ ሆነው በነሱ ላይ ሁለት አባላት እንዲጨመሩ በተወሰነው መሰረት ወ/ሮ ዓይናለም ተስፋዬና አቶ ሲሳይ ካሴ ተመርጠዋል።

6) **የማጠቃለያ ንግግር** (አቶ ፍቅሩ አበራ)

ስብሰባው ከመጠናቀቁ በፊት የእድሩ ዳኛ አቶ ፍቅሩ አበራ ባደረጉት የማጠቃለያ ንግግር የእድርን አስፈላጊነት ገልጸዋል። ለረጅም ግዜ ሲታሰብበት የቆየው የእድር ምስረታ በተግባር እውን ሲሆን ማየት

ለሁላችንም እጅግ የሚያስደስት ነው። ዛሬ እንዲህ ተገናኝተን ለመወያየት መብቃታችን እድር ምን ያህል በኅብረተሰባችን ውስጥ ተቀባይነት እንዳለው ያመለክታል። እናንተም ለወደፊቱ መደረግ አለበት ብላችሁ የሰጣችሁት አስተያየት ሁሉ ጠቃሚ ነው። እኛም ይህንን የህዝብ አስተያየት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የቻልነውን እናደርጋለን በማለት ገልጸዋል። በዚህ ቦታ ላይ ሆኖ ኅብረተሰቡን ማገልገል ቀላል እንዳልሆነ ማንም ሊገነዘብ ይችላል። ከፍተኛ ስሜትና ሙሉ ትጋትን ይጠይቃል። ይህ ደግሞ ለመስራት ሰዎች እራእይ ሊኖራቸው ይገባል። እራእይ ሲኖርም ብቻ ነው አንድ ነገር በታቀደ መንገድ ሄዶ ግቡን ሊመታ የሚችለው። ስለሆነም ይህንን የመሰለ ጠቀሜታ ያለውን እድር ለመገንባት ትብብር ያስፈልጋል። ሁላችንም ከተባበርን እድሩን ለከፍተኛ ቦታ ማድረስ እንችላለንና ሁላችንም የእድሩን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግና ኅብረተሰቡን ለመርዳት እንነሳ በማለት አሳስበዋል። በዕለቱ የተነሱትንም ገንቢ ሃሳቦች ሁሉ ኮሚቴው በድጋሚ ይመለከታቸዋል ካሉ በኋላ የህዝቡን ተሳትፎ አድንቀው ዝግጅቱ በዚሁ ተጠናቋል።

ስብሰባው በ6pm teTenaqual.

***ለለለለለለለለለለለለ ድድድድድድድድድድድድ ርርርርርርርርርርርር***

---

## ***ግዚያዊ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያከናወናቸው ተግባሮች፤***

የግዚያዊ ኮሚቴው አባላት ብዛት 8 ነው እነርሱም አቶ ፍቅሩ አበራ፣ አቶ እስማኤል ሲሊማን፣ አቶ ለማ ብሩ፣ አቶ ግርማ ፈይሳ፣ አቶ ስጦታው በፍቃዱ፣ አቶ ዳዊት ውብሸት፣ አቶ ወንድይፍራው ጎመራ፣ እና ስሎሞን ከበደ ናቸው። ያለማቋረጥ ተገናኝተው በመግባባት ሲሰሩ ቆይተዋል። ሌሎች አባላትም ሙሉ በሙሉ ባይመቻቸውም ባገኙት ግዜና አጋጣሚ ሁሉ ለምሳሌ አቶ ታሬ ኃይሌ፣ አቶ ሲሳይ ካሴና ወ/ሮ ዓይናለም ተስፋዮ ለተወሰኑ ግዜያት በስብሰባ በመገኘት ገንቢ ሃሳቦችን ስጥተዋል።

**በየወቅቱ የተደረጉት የስራ ክንውኖች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።**

**March 16, 2010 የተደረገ ስብሰባ**

ይህ የመጀመሪያው የእድሩ ስብሰባ የተደረገበት ቀን ሲሆን፡ በሚከተሉት ዋና ዋና ሃሳቦች ላይ ውይይት ተደርጓል፣

1. የእድሩን ዓላማዎች በግልጽ ማስፈር፤
2. መተዳደሪያ ደንብ ሁሉን አቀፍና ዝርዝሮችን በግልጽ ያሰፈረ ማዘጋጀት።
3. እድሩ የፖለቲካ፤ የጎሳ፤ የዘር፤ የኃይማኖት፤ የጾታ፤ የዜግነት ልዩነትን የማይመለከት ይልቁንም ሁሉንም በአንድነት የሚያቅፍ ሆኖ የሚቋቋም ነው። እስከዛሬ በሲድኒ ውስጥ እንዳየነው እነዚህ ልዩነቶች በሀዘን ቦታ እንዳልኖራቸውና ሁሉም ከየአካባቢው ግልብጥ ብሎ በመምጣት የሚሳተፍበት የሀዘንና የደስታ ግዜዎችን መለስ ብሎ ማስታዋሉ በቂ መረጃ ነው። ያም ታይቶ ባይታወቅ ኖሮ በማንኛውም ግዜ በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረት ትብብርን መጀምር ተገቢ እንደሆነ ታምኖበታል። መተዳደሪያ ደንቡም ይህንኑ ማንጸባረቅ እንዳለበት ተገልጿል።
4. ጅምሩን በማየት ብዙ ሰዎች እንዲመጡ ለማድረግ መንፈስ ጠንካራ ሆኖ መስራት። ስለሆነም የአባላት ቁጥር የሚበዛበትን መንገድ ሁሉ መጠቀም።
5. ቀላል የገንዘብ አከፋፈል ዘዴዎችን ማጥናት፡፡ በባንክ ቢሆን ይመረጣል ።

**<u>April 3/04/2010 የተደረገ ስብሰባ</u>**

1. የእድሩ መተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

**<u>May 2nd, 2010 የተደረገ ስብሰባ።</u>**

1. የአባልነት መመዝገቢያ ቅጽ ተዘጋጅቷል።
2. የእድሩን ድረ ገጽ ለመክፈት በዕቅድ ተይዟል።
3. በኮምዩንቲ ሬድዮ እድሩን ማስተዋወቅና ድረ ገጽ ላይ ማውጣት፣
4. የመተዳደሪያ ደንቡን ወደ እንግሊዝኛ የመተርጎም ስራ ተጀምሯል።
5. ግዚያዊ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ተቋቁሟል። በዚሁ መሰረትም፤

አቶ ፍቅሩ አበራ (ዳኛ), አቶ እስማኤል ኢብራሂም ( ም/ዳኛ), አቶ, ስጦታው በፍቃዱ (ም/ዳኛ), አቶ ግርማ ፈይሳ (ትሬዠረር), አቶ ለማ ብሩ (ገንዘብ ያዥ), አቶ ስሎሞን ከበደ (ፀሐፊ), አቶ ዳዊት ውብሸት (አባል), አቶ ወንድይፍራው ጎመራ (አባል), አቶ ሀብተወልድ ንጋቱ (አባል).

**<u>May 16, 2010 በተደረገ ስብሰባ</u>**

- ስለ እድሩ ዓላማና ለአባላት ስለሚሰጠው ጠቀሜታ በለአራት ገጽ መግለጫ ተዘጋጅቶ ታድሏል።
- ከMay 2nd ጀምሮ ቅጹና አጭር መግለጫው ተሰራጭቶ ቅጹን ሞልተው የተመዘገቡና የመጀመሪያውን ክፍያም የጀመሩ የሰዎች ዝርዝር እንዲዘጋጅ ታቅዷል። ገንዘብ ተሰብስቧል።
- የእድሩ መተዳደሪያ ደንብና ለአባልነት የማመልከቻ ቅጽ በኢትዮጵያ ኮምዩንቲ ማኅበር ድረ ገጽ ላይ ወጥቷል።

**<u>June 13, 2010 የተደረገ ስብሰባ</u>**

- የተመዘገቡና ገንዘብ የከፈሉ አባላት የስም ዝርዝር በመዝገብ ሰፍሯል።
- አቶ እስማኤል በኮምዩንቲ ሬድዮ ቀርበው ስለእድሩ መግለጫና ቃለ ምልልስ አድርገዋል።
- የእድሩ ፖስታ ሳጥን ተከፍቷል (**<u>POBox 279 Auburn, NSW 1835.)</u>**
- የገንዘብ ደረሰኝ ተዘጋጅቷል፡፡

**<u>July 4, 2010 የተደረገ ስብሰባ</u>**

- የአባላት የወር መዋጮ ክፍያን በተመለከተ ውይይት ተካሂዷል። የክፍያ አማራጮች መንገዶች ተጠንተው እንዲቀርቡ ተወስኗል።

**<u>July 31, 2010 የተደረገ ስብሰባ</u>**

- የባንክ አካውንት ተከፍቷል።

**August 29, 2010፣ Sept. 12, 2010 እና Oct. 10, 2010**

- በነዚህ ግዝያት ውስጥ ኮሚቴው ስብሰባ እድርጎ የተለያዩና ቀጣይ የሆኑ ተግባራትን አከናውኗል።

**የተለያዩ ቅጾች/ፎርሞች ተዘጋጅተዋል**

- የአባልነት ማመልከቻና የስምምነት ውል ቅጽ/ Application & Consent Declaration form/ ተዘጋጅቷል።
- የውክልና/ Proxy/ ቅጽ
- ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ቅጾች።

**ሌሎች ከእድር ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን በተመለከተ የሚከተሉት ይገኙበታል።**

- የኑዛዜ አዘገጃጀት ሂደትና ፎርም አሞላል/ Will kit/
- ለሞት ሰርተፊኬት ስለማውጣት/ Death certificate/
- የስም ቅያሬ/Change of name/
- ሌሎች/Others ለምሳሌ፤ በfuneral Directors አሰራር ላይ ቅሬታ ካለ እንዴት ለFairtrading ቅሬታ ማቅረብ እንደሚቻል።

ከዚህ ደብዳቤ ጋር የተላከሎት ካርድ የእርሶን መዝገብ ቁጥር የያዘ ነው። ባንክ ገንዘብ ሲከፍሉ ያንን ቁጥር ከእነስሞ ይጥቀሱ ከመዝገባችን ጋር በቀላሉ ማስተያየት ስለምንችል ስራችንን ያቀልልናል። ከእድሩ ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ይህ የርሶ መለያ ቁጥር ይሆናል። ስለሆነም በማንኛውም ግዜ ይጥቀሱት።

ስለ ገንዘብ አከፋፈል፣ ስለ እድሩ የአሰራር ሂደትና እስከዛሬ ስለተከናወኑት ወይም ስለማንኛውም እድር ነክ ጉዳይ አስተያየት ወይም ሃሳብ ካሎት በስልክ፣ በደብዳቤ፣ በኢሜል ወይም በግንባር ቀርበው ሊያነጋግሩን ይችላሉ።

ከምስጋና ጋር

የእድሩ አስተዳደር ጽ/ቤት